# አትክልት

IPMS ETHIOPIA



## የምርታማነት ማሻሻያና ገበያ ስኬት (IPMS) ፕሮጀክት የእሴት ሰንሰለት (value-chain) ማበልጸጊያ ተሞክሮዎች ጥንቅር

### መቅድም

ላለፉት ረጅም ዘመናት አትክልቶችን ውሃ ለማጠጣት ከወንዞችና ከምንጮች በተፈጥሮ ወንዝ ጠለፋ የምናገኘውን ውሃ ስንጠቀም ኖረናል፡ በደርግ ዘመነመንግስት በሰፋፊ እርሻዎችና አነስተኛ ይዞታ ባላቸው አርሶ አደሮች በተመሠረቱ የህብረት ሥራ ማህበራት አማካኝነት በመስኖ የሚለሙ የአትክልት ምርቶችን ለማስተዋወቅ ትላልቅ የመስኖ ልማቶች ተጀምረው ነበር፡፡

የደርግ መንግሥት ከወደቀ በኋላ በቤተሰብ ደረጃ የሚለሙ አነስተኛ የመስኖ ልማቶችን ለማስተዋወቅ ጥረት ተደርጓል፡፡ ውሃም ከግድብና ወንዞችን በመጥለፍ፣ ወይም ጥልቅ ከሆኑና ካልሆኑ ጉድጓዶች በእጅ ወይም በውሃ መሣቢያ ሞተሮች አጋዥነት በመሳብ መጠቀም ተችሏል፡፡

መንግስት እነዚህን ጥረቶች ለማጎልበት የተለያዩ የውሃ ምንጮችን በማልማት እገዛ አድርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መንግስት የውሃ ተጠቃሚ ማህበራትን በማቋቋም ለመስኖ ሥራ የሚያገለግሉ መሳሪያዎችን አቅርቧል፡፡ ከዚህ ሌላ አልፎ አልፎ ዘር አቅርቧል፡፡በ1998ዓ.ም በኢትዮጵያ የተመረተው የአትክልት መጠን ወደ 2.8 ሚሊዮን ቶን የሚገመት ሲሆን ከዚህ ውስጥ 21000 ቶን የሚሆነው ወደ ውጭ ተልኮ 4.8 ሚሊዮን ዶላር ገቢ አስገኝቷል፡፡ ይህንን ከጎረቤት ሀገር ጋር ስናወዳድር በተመሳሳይ ዓመት በኬንያ ወደ ውጭ የተላከ የአትክልት ምርት ወደ 178 ሚሊዮን ዶላር የሚገመት አስገኝቷል፡፡

# የእሴት ሰንሰለት ማበልጸጊያ ዘዴ



የምርታማነትና የገበያ ስኬት ማሻሻያ (IPMS) ፕሮጀክት ገበያ ተኮር የሆኑ የግብርና ምርቶችን ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ አሳታፊ የሆነ የእሴት ሰንሰለት ማበልጸጊያ ዘዴ ተጠቅሟል፡፡ ዘዴው በራሱ ሁሉን አቀፍ በመሆኑ በውስጡ ምርትን፣ የግብዓት አቅርቦትን፣ የግብርና አገልግሎቶችን፣ የግብይትና የንግድ ሥራ ድጋፍ አገልግሎትን በመያዝ ለውጥ የማምጣት አላማውን ለማሳካት ጥረት የሚያደርግ ነው፡፡ የገበያ ፍላጎትን መሠረት ያደረገና ዕውቀት መጋራትንና የንግድ ደንብን በመከተል የግልና መንግስታዊ ዘርፎችን የሚያሳትፍ ነው፡፡ ከዚህ ሌላ ዘዴው የፆታ እኩልነትና የአካባቢ ተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና ማሻሻያ ዘዴን ይከተላል፡፡ ይህ ዘዴ መመረት ያለባቸውን የምርት ዓይነቶች ይመርጣል፣የሚያጋጥሙ ችግሮችን ይፈትሻል፣ ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፡፡ የተገኘውንም ውጤት ይገመግማል፡፡

# የአትክልት የእሴት ሰንሰለት ፍተሻ

ከምርታማነትና ገበያ ስኬት ማሻሻያ (IPMS) ፕሮጀክት ከአስሩ የሙከራ ወረዳዎች ውስጥ በስድስቱ፣ ማለትም በአጽቢ፣ አላማጣ፣ ፎገራ፣ አድአ፣ መኤሶና አላባ የሚገኙ ባለድርሻ አካላት በመስኖ የሚለማ የአትክልት ምርት ቀዳሚነት ያለውና ለገበያ ተፈላጊ የሆነ ምርት መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በመተማ ወረዳ አትክልት ቅድሚያ የሚሰጠው ምርት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህ ቅድሚያ የመስጠት ሂደት ታሳቢ የሆኑ ቁልፍ ጉዳዮች ተለይተዋል፡፡ እነሱም ያለው የገበያ ፍላጎት፣ አርሶ አደሩ ስለገበያ ያለው ግንዛቤና ተሳትፎ፣ የሥነ ምህዳሩ ተስማሚነት፣ በተለይም ደግሞ የታቀዱ ወይም አሁን በሥራ ላይ ያሉ መስኖዎችና ውሃን የማልማት ሥርዓት ናቸው፡፡

በኢትዮጵያ የህዝብ ቁጥር መጨመርንና የአመጋገብ ሥርዓት ለውጥን ተከትሎ የአትክልት ፍላጎት እያደገ መጥቷል፡፡ በወረዳ ውስጥ የሚገኙ የአትክልት ገበያዎች በአብዛኛው ለትላልቅ ነጋዴዎች ወይም በወረዳና ከወረዳው ውጭ በሚገኙ ገበያዎች ለማድረስ በሚሰበስቡ የአካባቢ ነጋዴዎች የተሞሉ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ከአጽቢና ከአላማጣ የሚሰበሰቡት መቀሌ ለሚገኙት ትላልቅ ነጋዴዎች ያደርሳሉ፡፡ ፎገራ የሚገኙት ሰብሳቢዎች ለጎንደርና ለባህር ዳር ነጋዴዎች ያቀብላሉ፡፡ በአድአ የሚገኙት ለአዲስ አበባ ገበያ ሲያቀብሉ የአካባቢ ትናንሽ ገበያዎች ደግሞ ለአላባና ለመኢሶ ያቀርባሉ፡፡ ዋናው የግብይት ስልት የሚያተኩረው ባሉት ገበያዎች ውስጥ ዘልቆ በመግባት የገበያ ድርሻውን ማሳደግና ሌሎች አዳዲስ ገበያዎችንም መፍጠር መቻል ነው፡፡

ከላይ በተገለጹት ወረዳዎች ውስጥ የሚከተሉት የእሴት ሰንሰለት ተግዳሮቶች ሊስተዋሉ ችለዋል፡፡

- በመስኖ በመጠቀም አትክልትን የማምረት ሥራ ዕውቀትና ክህሎት ማነስና የድህረ ምርት አያያዝ ጉድለት፣
- ለአትክልት ምርት የሚያገለግሉ የዘር፣ የእርሻ ኬሚካሎች፣ የመስኖ መሳሪያዎችና የመሳሰሉት አቅርቦት በቂ አለመሆን፣
- የጋራ ጥቅም የሚሰጡ መስኖዎች አያያዝ ደካማነት፣
- ምርቱ ከወቅቶች መለዋወጥ ጋር የመቀነስና የመጨመር አዝማሚያ ስለሚያሳይ የዋጋ መዋዠቅ መፈጠሩ፣
- ጥቂት ነጋዴዎች ገበያውን የሚቆጣጠሩበት የገበያ ስርዓት በመኖሩ ብዙ አምራች ሻጮች ከጥቂት ገዢዎች ጋር ብቻ እንዲገበያዩ መገደዳቸው፣
- በመስኖ ልማት ተዋናዮችና በአምራቾች መሃል ያለ ግንኙነት አነስተኛ መሆን ወይም ምንም ግንኙነት/ትስስር ያለመኖር፣

ሰንጠረዥ 1 የአትክልት ገበያ

| | ያሉ ምርቶች | አዳዲስ ምርቶች |
|---|---|---|
| ያሉ ገበያዎች | ገበያ ውሰጥ ዘልቆ መግባት<br>ተጨማሪ አትክልትን መሸጥ (ሽንኩርት፣ ቲማቲም፣ ጎመን፣ ምርቶችን ላሉት ገበያዎች ማቅረብ) | ምርትን ማሻሻል<br>የሽንኩርት ዘር ማባዛትና በአካባቢው መሸጥ ከውጭ የሚገባውን ለመተካት |
| አዲስ ገበያ | ግብይትን ማሻሻል<br>ያለውን የአትክልት ምርት ለመሸጥ የሚያገለግሉ አዳዲስ ገበያዎችን ወይም መሸጫ ቦታዎችን መለየት | |

# የእሴት ሰንሰለትን ማበልጸግ



## የግብርና ኤክስቴንሽን

የአትክልት ምርትን ለማሻሻል ትልቅ እንቅፋት እየሆነ ያለው በወረዳ ደረጃ የዕውቀትና ክህሎት ማነስ መኖሩ ነው፡፡ አዲስ መንገድ በመጠቀም ክህሎትን የማጎልበትና ዕውቀትን ከምንጩ ለማግኘት የሚቻልበት መንገድ የማመቻቸት ተግባር ተካሂዶአል፡፡

## ክህሎትን ማዳበር

- በወረዳ ደረጃ በቂ ብቃት ያለው ባለሙያ ለማስገኘት ከወረዳ ውጭ ካሉ አሰልጣኞች ጋር ትስስር ወይም ግንኙነት ተፈጥሯል። በተለይ የመልካሳ ግብርና ምርምር ማዕከል (ለአድአ፣መኤሶ) በአማራ ክልል ደግሞ የአዴት ግብርና ምርምር ማዕከል (ለፎገራ) ተጠቃሽ ናቸው ፡፡
- የምርታማነትና ገበያ ስኬት ማሻሻያ ፕሮጀክት በብዙ አበረታች በሆኑ መንገዶች የኤክስቴንሽን ሠራተኞችንና የአምራቾችን ዕውቀትና ሙያን ለማሻሻል የሚጥር ቢሆንም እንደ ረጅም ጊዜ ዕቅድ ግን መወሰድ ያለበትና ትኩረት የሚገባው በመስኖ ሥራና በአትክልት ልማት ልዩ ትምህርት የወሰዱና የሰለጠኑ ባለሙያዎችን ለማፍራት ኃላፊነት የተጣለበት የትምህርት ማዕከል መገንባት ነው፡፡
- አለም አቀፍ የውሃ አስተዳደር ተቋም (IWMI) የፕሮጀክቱ አጋር በመሆን የክልሉንና የወረዳውን (በአድአ፣ በመኢሶ፣ በመተማ) ባልደረቦች አቅም ለመገንባት ባዘጋጃቸው መደበኛ ባልሆኑ ስልጠናዎች ብዙ አርሶ አደሮች ከሰለጠኑ በኋላ ከሠራተኞችና ከሌሎች አርሶ አደሮች ጋር በመሆን ሙያቸውን ሊያዳብሩ ችለዋል፡፡
- በክፍል ውስጥ የሚደረጉ ስልጠናዎች በርካታ አርሶ አደሮች ዕውቀትን ሊያገኙ በሚያስችል መልኩ በመስክ ስልጠና ይታገዛሉ፡፡ ፕሮጀክቱ ከዓለም አቀፍ የውሃ አስተዳደር ተቋም (IWMI) ጋር በመሆን በእርሻ ሥራና በውሃ አጠቃቀም ሥርዓት ላይ የማሰልጠኛ መመሪያዎችን አዘጋጅቷል፡፡
- አንዳንድ የፕሮጀክቱ የሙከራ ወረዳዎች በሴቶች ላይ ልዩ ትኩረት አድርገዋል፡፡
- የተሰጡት ስልጠናዎች አሳታፊ ገበያ ተኮር የኤክስቴንሽን ዘዴን አጠቃቀም፣ የሥርዓተ ፆታና ኤች አይ ቪ ኤድስን ኤክስቴንሽንና ፈጣን የገበያ ጥናት ናቸው፡፡ በተጨማሪም ፕሮጀክቱ ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎች በነዚህ አርዕስቶች ዙሪያ ወደፊት ትምህርቱን ለማሳደግና ለማሰራጨት ሊጠቅሙ የሚችሉ ጽሑፎችን አዘጋጅቷል፡፡
- የመስኖ ሥራ እየተስፋፋ ሲሄድ የውሃ መሣቢያ ሞተሮች መጠቀምም እያደገ ይሄዳል፡፡ ነገር ግን በመንደር ደረጃ የተቋቋሙ የፓምፕ መጠገኛ ቦታዎች የሉም፡፡ ስለዚህ ፕሮጀክቱ በአንዳንድ ወረዳዎች (በአጽቢና በፎገራ) የውሃ መሣቢያ ሞተር ለሚጠቀሙ አርሶ አደሮችና ጠጋኞች ስልጠናዎች እንዲሰጡ አድርጓል፡፡

## የእውቀት አስተዳደር

- ፕሮጀክቱ ከግብርና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የኢትዮጵያ የግብርና ፖርታል (www.eap. gov.et) አዘጋጅቷል፡፡ ሌሎች መረጃዎችን ጨምሮ ይህ ፖርታል የመስኖ አትክልት አመራረት ጽሁፎችን የግብይትና የንግድ አገልግሎቶችን ከሌሎች የማሰልጠኛ ፅሁፎች ጋር ጨምሮ ይዟል፡፡ ፕሮጀክቱ የኢንተርኔት ተደራሽነትን በማሥፋፋት የስልክ መስመር ለገባላቸው ቦታዎች በወረዳ የዕውቀት ማዕከላት በኩልና በአርሶ አደሩ ማሰልጠኛ ማዕከሎች በኩል እንዲመቻች አድርጓል፡፡ የስልክ መስመር ለሌላቸውና የኢንተርኔት ግንኙነት መፍጠር ባልተቻለባቸው ወረዳዎች የፖርታሉ ቅጂ በDVD እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡
- የመስኖ ግብርና ፍላጐት እንዲጨምር ወይም ግንዛቤ እንዲሰፋ ለማድረግ ፕሮጀክቱ ለአምራቾችና ለግብርና ባልደረቦች እንዲሁም ለአስተዳዳሪዎች የተሻሻሉ በመስኖ የሚለሙ የአትክልት ምርቶች ባሉበት በተለይ እንደ ዝዋይ፣ መቂ ያሉ አካባቢዎችና የጀነሲስ እርሻ ድርጅት በደብረዘይት አካባቢ ጉብኝት አመቻችቷል፡፡ ቀጥሎም ቁልፍ የሆኑ የፕሮጀክቱ አጋሮች በመስኖ ሥራው ውጤታማ የሆኑትን የፕሮጀክቱ ሙከራ ወረዳዎች ጐብኝተዋል፡፡
- በየጊዜው በተለያየ መንገድ የሚገኙ ትምህርቶችን ለማግኘትና ለማስፋፋት ፕሮጀክቱ የድህረ ምረቃ ተማሪዎችን በመደገፍ የምርምር ጽሑፋቸውን በመስኖ በሚለሙ አትክልቶች ዙሪያ እንዲሰሩና ጥናታቸውንም ባካሄዱበት አካባቢ ሴሚናሮችን በማዘጋጀት ግኝታቸውን ለሚመለከታቸው አካላት እንዲያካፍሉ አድርጓል፡፡
- ዕውቀትን በተፈለገ ጊዜ ለማግኘት በሚቻል መልክ ለማስቀመጥና ለመያዝ እንዲሁም ለብዙሃን ታዳሚዎች ለማድረስ ፕሮጀክቱ በአላማጣ “በሽንኩርት ግብይት” ላይ አጠር ያለ የቪዲዮ ፊልም አዘጋጅቷል፡፡



## ከእሴት ሰንሰለት ተዋናዮች ጋር ያለው ትስስር

የወረዳው ኤክስቴንሽን ሠራተኞችና የፕሮጀክቱ ባልደረባዎች ከግብአት ወይም አገልግሎት አቅራቢያዎችና የገበያ ድርጅቶች ጋር ከታች በተመለከተው መሰረት ትስስር እንዲኖር አድርጓል፡፡

## የግብይት ማሻሻያ አሰራሮች

- የፕሮጀክቱ የግብይት ማሻሻያ አሰራሮች የሚከተሉትን ይጨምራል
- የግብይት ግልፅነት እንዲኖር የሚወሰዱ እርምጃዎችን
- በአካባቢ ደረጃ የሚገኘውን የጋራ የግብይት ሁኔታዎች ማጠናከር
- የድህረ ምርት የማከማቻ ዘዴንና የማቀነባበር ቴክኖሎጂን ማስተዋወቅ



የገበያ አቅምን በሚገባ ለመረዳት ፕሮጀክቱ ከገጠር ልማት መስሪያ ቤቶች ባልደረባዎች ጋር፣ ከተማሪዎችና የክልል ምርምር ተቋሞች ጋር በመተባበር የእሴት ሰንሰለት የዳሰሳ ጥናቶችን አድርጓል፡፡ የጥናቶቹ ውጤቶች የግብይት አሰራርን ለማሻሻል ረድተዋል፡፡

## የግብይት ግልፅነት እንዲኖር የሚወሰዱ እርምጃዎች

ብዙ ጥናቶች እንደሚያመለከቱት የአርሶ አደሮችን ምርት የሚገዙት ጥቂት ነጋዴዎች በመሆናቸው ምክንያት፤አርሶ አደሮች በአብዛኛው ዋጋ ተቀባይ ናቸው፡፡ ስለዚህ ፕሮጀክቱ አምራቾችና ነጋዴዎች የሚገናኙበት መድረክ በማዘጋጀት አርሶ አደሮች አቅም ካላቸው ገዥዎች ጋር ግንኙነት እንዲፈጥሩና ለተሻለ ዋጋ እንዲደራደሩ ዕድል ፈጥሮላቸዋል፡፡ የገበያ ግልፅነቱ የበለጠ እንዲጠናከር ለማድረግ ፕሮጀክቱ የገበያ መረጃን በማስታወቂያ ሰሌዳ ወይም በሬዲዮ በማስተዋወቅ ድጋፍ አድርጓል፡፡ አምራቾች ከተጨማሪ አዳዲስ ገበያዎች ጋር ትስስር እንዲኖራቸው (በተለይ በፎገራና በአላማጣ) በማድረግ የገበያ አድማሳቸውን አስፍቶአል፡፡ በአድአ የሚገኙ አርሶ አደሮች የተሻለ ዋጋ ለማግኘት ሞባይል ቴሌፎናቸውን ይጠቀማሉ፡፡

## በየአካባቢው የጋራ የግብይት ሥራዎችን ማጠናከር

የአርሶ አደሩን የመደራደር አቅም የበለጠ ለማጎልበት የፕሮጀክቱ አጋሮች ለጋራ የግብይት አሠራሮች ድጋፍ በመስጠት ምርቱ በአንድ ማዕከል እንዲከማች አድርገዋል፡፡ በአላማጣ እንዲህ አይነቱ ሥራ በህብረት ሥራ ማህበር አማካኝነት ይከናወናል፡፡ የአላማጣ የህብረት ሥራ ማህበር የአትክልት ምርቶችን ግዥና ሽያጭ እንዲፈፅም ጥረት ቢደረግም ውጤታማ አልሆነም፡፡ ይሁንና ቀስ በቀስ ነጋዴዎች ከአካባቢው ሽንኩርት አምራቾች ማህበራት ጋር በመወዳደር የተሻለ ዋጋ ለማቅረብ ችለዋል፡፡

## ድህረ ምርት የማከማቸትና የማቀነባበር ዘዴ

ፕሮጀክቱ ምርት ከእርሻ ላይ ከተነሳ በኂላ የሚደርስበትን ብልሽት ለመከላከል እንዲቻል የድህረ ምርት ማከማቻ ቴክኖሎጂዎችን አስተዋውቋል (በአላማጣ)፡፡ አላማውም ምርቱ ሳይበላሽ ረጅም ጊዜ እነዲቆይ ለማድረግ ነው(ለምሳሌ ሽንኩርት)፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በባህርዳርና በፎገራ ፕሮጀክቱ አነስተኛ የቲማቲም ጭማቂ ማቀነባበሪያ አስተዋውቋል፡፡





## ምርት ማሻሻያ ድጋፎች

በመስኖ የሚለማ የአትክልት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚከተሉት ጉዳዮች ትኩረት ተሰጥቷቸዋል ።

- በመስኖ የሚለማ የአትክልት ቦታን ማስፋት
- የእርሻ አሠራርን ማሻሻል



አሁን ያለው ለመስኖ የምንጠቀመው የውሃ ሀብት በሁለት ሊከፍል ይችላል። የመጀመሪያው በጠለፋ ልንገለገልበት የምንችልና ሁለተኛው በተለያዩ የውሃ መሳቢያ መሳሪያዎች ልንጠቀምበት የምንችለው ነው። የሁለቱም የመስኖ ሥራ ማሻሻያ ድጋፎች ዋና አላማ የመስኖ ልማቱን ቦታ ለማስፋትና ምርትና ምርታማነትን ለማሻሻል ነው።

### በመስኖ የሚለማ አትክልት ቦታን ማስፋት

በተፈጥሮ ስበት የሚገለገሉ

- አጋር ድርጅቶች በተለያየ የክልል ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ የመሳሰሉት በውሃ ሀብት መስኖ ልማት ላይ ከፍተኛ መዋዕለ ነዋይ በማፍሰስ በመስኖ የሚለማ የአትክልት መሬት ስፋት እንዲጨምር አድርገዋል፡፡ የዚህ አይነቱ የማስፋፊያ ሥራ በተለይ በአጽቢ የቀድሞውና የአሁኑም የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ላይ በተደረገ የመዋዕለ ንዋይ ፍሰት የተነሳ ለብዙ ውሃ መፍለቅ ምክንያት ሊሆን ችሏል፡፡
- በፕሮጀክቱ አጋሮች አማካኝነት የወንዝ ጠለፋን በመጠቀም አዋጪ ያልሆኑ ሰብሎችን በመስኖ በሚለሙ አትክልቶችና ከፍተኛ ዋጋ በሚያወጡ ሰብሎች የመተካት ሥራ በተለያዩ ወረዳዎች በመስፋፋት ላይ ነው። ለምሳሌ በአላማጣ ከጥራጥሬ ወደ አትክልት ምርት፣ በአጽቢ የወንዝ ውሃ ጠለፋና በተፈጥሮ ስበት መስኖ ሥራ ሲጠቀሱ፣ በአድአ የጎዲኖ ሽፋን ከቅባት እህሎች ወደ አትክልት ምርት የተደረጉ ለውጦች ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ በመሬት አጠቃቀም ላይ እየተደረገ ያለው ለውጥ ሊመጣ የቻለው በፕሮጀክቱ የማሻሻያ ሥራ እንቅስቃሴ አማካኝነት መሆኑ እሙን ነው፡፡

### የውሃ መሳቢያ መሳሪያ ተጠቃሚነት

ፕሮጀክቱ የመስኖ አትክልት ማምረቻ መሬት ማስፋትን ለማገዝ ካሉት የውሃ ሀብቶች በተሻሻሉ ዘዴዎች ውሃ መሳብን ይደግፋል። ለምሳሌ በአላማጣ አገልግሎት ያቋረጡ የውሃ ጉድጓዶችን እንደገና እንዲያንሰራሩ ማድረግ ሊጠቀስ ይችላል። እንደዋና የማሻሻያ ድጋፍ ተደርጐ የሚወሰደው ደግሞ በሁሉም የሙከራ ወረዳዎች ከወንዞች ለውሃ መሳቢያነት የሚያገለግሉ ሞተሮችን ማስተዋወቁ ነው። ከነዚህ የውሃ መሣቢያ ሞተሮች አንዳንዶቹ ፕሮጀክቱ በዘረጋው የብድር አገልግሎት የተገኙ ናቸው (ለምሳሌ አድአ)፤ ሌሎቹ ደግሞ በአርሶ አደሩ በራሱ የተገዙ ናቸው(ለምሳሌ አድአ፣ መኤሶ፣ መተማ)። አንዳንዶቹ ደግሞ በመንግስት ድጋፍ ወይም በእርዳታ ድርጅቶች የተሰጡ ናቸው (ለምሳሌ አጽቢ፣መተማ፣ፎገራና፣አድአ)፤ ፕሮጀክቱ የመስኖ ሥራን ለማገዝ ከአነስተኛ ጉድጓዶች፣ የሚገኘውን ውሃ መጠቀም እንዲቻል የጉድጓዱ ግርግዳ እንዳይፈርስ በተሻለ ሁኔታ አስገንብቷል።

### የእርሻ ሥራዎችን ማሻሻል

የፕሮጀክቱ አጋሮች ምርታማነትን ለማሳደግ የሚረዱ የተሻሻሉ ዝርያዎችን፣ የተሻለ የእርሻ አያያዝን (የድርብ መስመር አዘራርን፣ አፈራርቆ መዝራትን) የመሳሰሉትንና እንዲሁም የተሻለ የውሃ አጠቃቀም ዘዴን አስተዋውቋል። ለምሳሌ በአላማጣና በአድአ ውሃን በማጥለቅለቅ መልክ ሳይሆን በቦይ ማስኬድ ተጠቃሽ ነው።



### የግብአት አቅርቦትና የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ድጋፍ

የመንግስትና የግሉ ዘርፍ ሁለቱም ለመስኖ አትክልት ልማት ግብአትና የተለያዩ አገልግሎቶችንና የመስኖ መሳሪያዎችን ጭምር ያቀርባሉ። የሚያጋጥሙ ችግሮች እንደቦታው የሚለያዩ ቢሆንም የሚከተሉት የማሻሻያ አሰራሮች ተተግብረዋል።

- የተሻሻሉ የአትክልት ዘሮች ወይም ችግኞች አቅርቦት
- የእርሻ ኬሚካሎች አቅርቦት
- የመስኖ መሳሪያዎች አቅርቦትና ጥገና

### የተሻሻሉ የአትክልት ዘሮች ወይም ችግኞች አቅርቦት

- በአንዳንድ ወረዳዎች እንደ ፎገራ፤ መኤሶና፣አላማጣ ባሉት የተሻሻሉ ዘሮች አለመኖር በተለይ የሽንኩርት ዘር መታጣት እንደ ዋነኛ ችግር ይጠቀሳል። በአጽቢም የነጭ ሽንኩርት ችግኝ አለመኖር ስራውን ለማስፋፋት እንደ ችግር የሚታይ ጉዳይ ነበር፡፡
- በፎገራና በመኤሶ የሽንኩርት ዘር የማምረት ሥራ ሊበረታታ የቻለው ከፍተኛ ሽንኩርት አብቃይ ወደሆኑት እንደ ዝዋይ የመሳሰሉት ቦታዎችን የግል ኢንተርፕሬነሮች ባደረጉት የጉብኝት ሂደት ነው። ከዚህ በኂላ ዘር አምራቾች ከእርሻ ምርምር ተቋማት፣ ከምርታማነትና ገበያ ስኬት (IPMS) ፕሮጀክት የስራ ባልደረቦች ጋር በሚያደርጉት ምክክር የሽንኩርት ዘር የማምረት ክህሎታቸውን ማሻሻል ችለዋል። ለዘር ማምረት የሚያገለግለው ሽንኩርት ኮረት (bulb) በፎገራ አመቱን በሙሉ የማይገኝ በመሆኑ በአገሪቱ ባሉ ሌሎች ከተሞች ተፈልጐ እንዲገዛ አርሶ አደሮቹ ራሳቸውን በማደራጀት ተንቀሳቅሰዋል። አንዴ ዘሩ ከተመረተ በኂላ ፕሮጀክቱና አጋሮቹ በወረዳው ይሁን ከወረዳው ውጭ

ከገዥዎች ጋር ትስስር እንዲፈጠር አመቻችተዋል፤ በክልሉ የሚመለከታቸው አካላት ደግሞ ዘሩን በመሞከር ሕጋዊነት እንዲያገኝ አድርገዋል።

## የእርሻ ኬሚካሎች አቅርቦት

- ፕሮጀክቱ ከአምራቾችና ከግል ወይም ከአገልግሎት ኅበረት ሥራ ማህበራት የማዳበሪያና ሌሎች የእርሻ ኬሚካሎች አቅራቢዎች ጋር ትስስር እንዲፈጠር አድርጓል፡፡ ነገር ግን እነዚህን ግብአት አቅራቢዎች ለማጠናከር አልተንቀሳቀሰም፡፡

## የመስኖ መሳሪያዎች አቅርቦትና ጥገና

- በመስኖ መሳሪያዎች አቅርቦት በኩል ሁለቱም የመንግስትና የግሉ ዘርፍ ተሳታፊ ናቸው፡፡ አነስተኛ ዋጋ ያላቸው የውሃ መሳቢያ መሳሪያዎችን በማቅረብ በኩል የመንግስት ተሳትፎ ከፍተኛ ነው፡፡ በሞተር የሚሰሩ የውሃ መሣቢያ መሳሪያዎችን በማቅረብ በኩል መንግስት፣ የእርዳታ ድርጅቶችና የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ አላቸው፡፡ ፕሮጀክቱ የውሃ መሳቢያ ሞተሮችን ለማቅረብ ለአድአ ገበሬዎች ብድር አመቻችቷል። ከግሉ ዘርፍ ጋር ትስስር እንዲፈጠርም አድርጓል፡፡
- በአንዳንድ ወረዳዎች በተለይ በአጽቢና በፎገራ የውሃ መሣቢያ ሞተር ጥገናና አያያዝ ላይ ስልጠና እንዲሰጥ ከማድረጉም በላይ ቀደም ሲል ከተቋቋሙ ድርጅቶች ጋር ትስስር እንዲፈጠር በር ከፍቷል፡፡

# ሊለኩ የሚችሉ ተጨባጭ ውጤቶች

## ምርት፣ ምርታማነትና ገቢ

በፕሮጀክቱና በፕሮጀክቱ አጋሮች በጥምረት የተደረጉ የማሻሻያ ሥራዎች በወረዳዎች በመስኖ የሚለሙ አትክልቶች ልማት ማስፋፋት ላይ ከፍ ያለ አዎንታዊ ተፅዕኖ ለማድረግ ተችሏል። እነዚህ መስፋፋቶች በእያንዳንዱ ቤተሰብ ደረጃም ይሁን በወረዳ ደረጃ በተጨባጭ የሚታዩ ናቸው። በ2002 ዓ.ም በቤተሰብ ደረጃ በተሻሻሉ የመስኖ አትክልት ምርቶች ዙሪያ በፕሮጀክቱ በታቀፉና ባልታቀፉ ቤተሰብ መካከል ያለውን ልዩነት ለማወቅ ጥናታዊ ዳሰሳ ተደርጓል። በዚህም መሰረት በቤተሰብ ደረጃ በመስኖ የለማው መሬት ስፋትና የገቢ መጠን ልዩነት አሳይቷል። ልዩነቱም በሰንጠረዥ 1 እስከ 3 ባሉት ላይ ተመልክቷል።

## የግብአት አቅርቦትና ግብይት

በመስኖ ለሚለሙ አትክልቶች መስፋፋት ጉልህ አስተዋፅኦ ያደረጉ ሁለቱ የግብአት አቅርቦት አሰራሮች የመጀመሪያው የመስኖ መሳሪያዎች አቅርቦት ሲሆን ሁለተኛው የተሻሻለ የሽንኩርት ዘር ማምረት ናቸው።

በመስኖ መሳሪያዎች አቅርቦት በኩል የፕሮጀክቱ አሰራር የተወሰነ ነበር፤ ምክንያቱም አስቀድሞ በመንግስትና በእርዳታ ድርጅቶች በርካታ ጥረቶች በመደረጋቸው። ፕሮጀክቱ በመስኖ መሳሪያዎች የጥገና አገልግሎ አዋጭነት ላይ መረጃ እየሰበሰበ ነው።

በአድአ የግል የውሃ መሳቢያ ሞተር ኦፕሬተሮች በአጎራባች ለሚገኙ አርሶ አደሮች ወይም የቡድን አባላት በክፍያ ውሃ የመሳብ አገልግሎች እንዲሰጡ የተደረገው ጥረት ውጤታማ አልነበረም። ምክንያቱም አብዛኛዎቹ ገበሬዎች ከአትክልት ምርት በተገኘ ገቢ የራሳቸውን ውሃ መሣቢያ ሞተር የመግዛት አቅም ፈጥሮላቸዋል።

ምንም እንኳ ክፍያ ዝቅ የማለት ሁኔታ ቢታይበትም የአትክልት ምርት እሴት ሰንሰለትን ለማሻሻል በፕሮጀክቱ ከተከናወኑ እጅግ አስፈላጊ የግብአትና የአገልግሎት ሥራዎች ውስጥ በአከባቢ የሽንኩርት ዘር የማምረት ሂደት ነበር። ይህ ሪፖርት ሲዘገብ በፎገራ የነበረው ጥቅል የሽንኩርት ዘር ግብይት መጠን 3.4 ሚሊዮን ብር ነበር። ዘሩም በወረዳው ውስጥም ከወረዳው ውጭም ይሸጣል። እንዲሁም በመኤሶ አንዳንድ አርሶ አደሮች የሽንኩርት ዘር ማምረት ጀምረዋል።

## ሥርዓተ ፆታ

በአድአ ወረዳ በአትክልት የእሴት ሰንሰለት ዙሪያ የሴቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ እንዲቻል በሴቶች የክህሎትና እውቀት ማሻሻያ ላይ ትኩረት ተደርጓል። የሴቶች የመስክ ቀን በሴቶች ጉዳይ ላይ ያተኮረውን የልማት አካሄድ የበለጠ ለማስፋፋት ረድቷል።

በቡሬ፣ በአላማጣና በፎገራ አንዳንድ ሴቶች በጓሮአቸው ዘር የማፍላት በተለይ የበርበሬ ዘር ማምረትና ለጎረቤቶቻቸው በመሸጥ ተንቀሳቅሰዋል።

በፎገራ አነስተኛ የቲማቲም ጭማቂ የማዘጋጀት ሂደት ውስጥ ሴቶችን ለማሳተፍ የተደረገው ጥረት ውጤት አላመጣም። ምክንያቱም በቂ የገበያ ፍላጎት አልተገኘም።

## የአካባቢ ጥበቃ

በአድአ ወረዳ በመስኖ አትክልት ልማት የተነሳ አንዳንድ በስነ ምህዳር ላይ የደረሱ አሉታዊ ሁኔታዎች ተስተውለዋል። በተለይም በአትክልት ላይ የተረጩ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ብዙ ንቦችን ለሞት ዳርጓል።

## ተዋናዮችና ተሳታፊነት

አዳዲስ የአትክልት የዕሴት ሰንሰለት ተዋናዮች ተፈጥረዋል። በዚህም አዳዲስ ተሳታፊዎችም ታይተዋል።



ሥዕል 1



ሥዕል 2



ሥዕል 3







# ምርትን ለማሳደግና ስርጭቱን ለማስፋፋት አስተምህሮት፣ ተግዳሮቶችና ጠቃሚ አስተያየቶች

## የልማት አካሂድ-ኤክስቴንሽን

አዲሱ የኤክስቴንሽን አካሄድ የአትክልት የእሴት ሰንሰለት ባለድርሻ አካላት በየወረዳው የአሰራር ፍተሻ አድርገው በግብይት፣ በግብዓት አቅርቦትና በምርት ላይ ለየወረዳው ተስማሚ የሆኑ የማሻሻያ አሰራሮችን ለማዘጋጀት እንዲችሉ ረድቷል፡፡

የመስኖ አትክልት ምርታማነትን ለማሻሻል መንግሥታዊ በሆኑ ዘርፎች በመስኖ ለሚለሙ አትክልቶች ላይ የሚሠሩ የሰው ሀይል አቅም ግንባታ ላይ የሚፈሰው መዋዕለ ንዋይ አነስተኛ በመሆኑ የተሻለ ምርታማነት ለማምጣት ትኩረት ተሰጥቶበት የበለጠ መበረታታት ይኖርበታል፡፡

የመስክ ጥናታዊ ጉብኝቶች በመስኖ የሚለሙ አትክልት የማልማት ፍላጎትን ለመጨመርና የሽንኩርት ዘር ምርትን ለማሳደግ አይነተኛ መሳሪያዎች ነበሩ፡፡ ምክንያቱም አርሶ አደር ለአርሶ አደር የሚደረገው የሙያና የዕውቀት መጋራት የአጋርነት መልክ ስላለው በመስኖ የሚለማ አትክልት ምርትን ለማሻሻል ጠቃሚ ዘዴ ነው፡፡

## ግብይት

ዝቅተኛ ዋጋንና የዋጋ መዋዠቅን ልንዋጋ የምንችለው ከፍተኛ የሆነ የገበያ ግልፅነት ሲኖር ነው፡፡ (መረጃ ማግኘት፣በጋራ መስራት፣ ትስስር መፍጠር) ምርትን አቅዶ መስራትና የድህረ ምርት ማከማቻና አያያዝ ዘዴ ማሻሻል ያስፈልጋል፡፡

ብሔራዊ የግብይት መረጃ አቀራረብ ሥርአትን በመጠቀም አስቀድሞ የተለያዩ አትክልቶች በመስኖ የሚያመርቱ አካባቢዎች በቀጣይ ምን ማምረት እንዳለባቸው ማቀድ አስፈላጊ ነው፡፡

## ሥርዐተ ምርት

የመንግስት ዘርፍ ለመስኖ ልማት ሥራ የሚያገለግሉ መሰረተ ልማቶችን ማካሄድና የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤን ማሳደግ የመስኖ አትክልት ልማቱን ስለሚረዳ አስፈላጊ ሥራ ነው፡፡

የግሉ ዘርፍ በውሃ መሳቢያ መሣሪያዎች አቅርቦት ስራ ላይ መሳተፍ አዋጭ የሆነ የማሻሻያ ድጋፍና በመስኖ የሚለማ አትክልት ሥራን ለማስፋፋት የሚረዳ ነው፡፡ አነስተኛና ጥቃቅን የብድርና የቁጠባ ተቋማትም ይህንኑ በአሠራራቸው ውስጥ ማካተት አለባቸው፡፡

የተሻሻሉትን አዲስና የተለያዩ የሽንኩርት ዝርያዎችን መጠቀም፣ ማለትም እንደድሮው በኮረት ሳይሆን ከዘር የሚባዙትን መጠቀም ለመስኖ ሽንኩርት ልማት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡

## ግብአት

የሽንኩርት ዘርን በግሉ ዘርፍ ማባዛት አዋጭ የሆነ የኢኮኖሚ ጠቀሜታ አለው፡፡

ዘሩን ለማባዛት የጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት ከምርቱ አካባቢ ባሻገር ገበያውን ለማስፋት አስፈላጊ ነው፡፡

አነስተኛና ጥቃቅን የንግድ ዘርፎች ለመስኖ አትክልት የሚሆን አስፈላጊግብአት ማቅረብ ይችላሉ፡፡



